# ሞኝን እባብ ሁለቴ ይነድፈዋል

በዚች አጭር ጽሁፍ ለማቅረብና ለማስረዳት የምፈልገው በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን አገር አቀፍ ምርጫ አስመልክቶ የቀድሞ ከፍተኛ የወያኔ የአመራር አባል የነበሩ በወያኔ አመራር ውስጥም በተፈጠረ እርስ በርስ ግጭት ከነበሩበት ድርጅትና ሥልጣን ከተባረሩ በኋላ ዛሬ የቀድሞ የበረሃ ጓዳቸውን ተቃዋሚው ነን ብለው በመንቀሳቀስ የሚታወቁትን ግለሰቦችንና ቡድናቸውን ይሆናል ። እነዚህ ግለሰቦች የሰፊውን ህዝብ ትግል ተቀላቅለናል በማለት ባወጁት ዓዋጅ የተፈጠረውን አለመግባባትና ግርግር በተረዳሁት መጠን በአጭሩ ለመዳሰስ እሞክራለሁ ።

የተነሳሁበትን ዓላማ መሰረት ለማስያዝ "ይቅርታ" እየተባለ በየ ሬዲዮው ፣ በየድረገጹና በየፓልቶኩ ሁሉም እንደመሰለው የሚተረጉመውንና የሚተነትነውን እኔም ለኔ ትክክለኛ የመሰለኝን የግል ግንዛቤዬን ለአንባቢያን ለማካፈል ነው ።

በእርግጥ ይቅርታ በአግባቡ ከተጠየቀና በዳይ የተባለው ግለሰብ ወይንም ቡድን ተበዳዩን ክፍል በቀድሞ አድራጎቱና ሥራው መፀፀቱን ገልፆ ፣ መፀፀቱንም በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም አስመስክሮ ማሳየት ከቻለ ይቅርታው እንደ ግለሰቡ ወንጀልና አድራጎት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ይቅርታ ሊደረግለት አግባብነት አለው የሚል የግል እምነት አለኝ ።

ነገር ግን ሥልጡን ፖለቲካ እያሉ ተበዳዩንና ይቅርታ ልጠየቅ ይገባኛል የሚለውን ክፍል በማደናቆር ምንም የሚገኝ መፍትሄ አይኖረውም ። ሥልጡን እያሉ ሳይሰሩ ለመሰልጠን መሞከር ፤ ሳይማሩና መጸሐፍ በደረሰበት ሳይደርሱ እውቀት ለመሸመት መሞከር ፤ አሊያም ሳይታገሉ ነፃነትን መመኘት አይነት ይሆናል ።

በፖለቲካው ሰልጥነናል አሊያም የሰለጠነ ፖለቲካ ነው የምናራምደው ከተባለም ፣ ብዙዎቻችን በሰለጠነው ዓለም ነውና የምንኖረው ሥልጡን ፖለቲካ ምን ማለት እንደሆነና ምን እንደሚመስል በጥቂቱም ቢሆን የሚገባንና የተረዳነው ይመስለኛል ። እንደሰለጠኑትማ ሰልጥነን ፖለቲካውንም በሰለጠነ ሁኔታ እናራምድ ካልን ፣ እነዚህ ግለሰቦች አይደለም የፖለቲካ ቡድን ሊቀላቀሉ ፣ ይባስ ብሎም በአመራር ደረጃ ሊቀመጡ ይቅርና መኖሪያቸው የሚሆነው የሙት ይፍታህ ተፈርዶባቸው ቀሪው እድሜያቸውን የሚያሳልፉት በእስር ቤት ነበር የሚሆነው ።

ነገር ግን እነዚህ ግለሰቦች ባጋጣሚ ሥልጡን የሆነ ፖለቲካ የሚራመድበት አገር ላይ ስላልሆኑ የሚያራምዱትም የይስሙላ እንጂ እውን ስልጡን ፖለቲካ ባለመሆኑ ዛሬ እነሱ በፈፀሙትና በቀድሞ ተግባራቸው ይመዘኑ ቢባል ወይንም በሰለጠነው ዓለም ነዋሪ ቢሆኑ ሊገጥማቸው የሚችለው እጣ ፈንታ ሳይታለም የተፈታ ነው ። በመሆኑም በጣም እድለኞች ናቸው ብል እምብዛም ከስህተት ላይ አይጥለኝም ብዬ አምናለሁ ።

ግለሰቦቹ ዛሬ የተጠየቁት ባለፈው በስልጣን ዘመናቸው በሀገርና በህዝብ ላይ የፈጸሙትን በደል አምነው ፤ ለፈጸሙትም ወንጀል ከልብ ተፀፅተው የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ይጠይቁት ነው የተባለው ። እነሱ ግን ይቅርታም ለመጠየቅ ይሁና አለ ይቅርታው ማንሳት ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም ። ከአንዳንድ ደጋፊዎቻቸው ጆሮ ከሚያደነቁር ብለዋል ፤ አስበዋል ፤ ተመልሰዋል እያሉ በስማ በለው ከሚያስተጋቡት በቀር ይሄ ነው ተብሎ የሚነገርና የሚለካ የይቅርታ አዝማሚያ ከግለሰቦቹ ይገኛል ማለት ከላም ጥቁር ወተት ይታለባል ብሎ እንደመገመት እየሆነ መጥቷል ።

በሰለጠነው ዓለም በሀገር ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈፀመ ፤ አገር ለማስገንጠል የተባበረ እናም የመሳሰሉ ከባድ ወንጀሎችን የፈፀመ ይቅርና በሚስቱ ላይ ሌላ ሴት ሄዷል ፣ ወይንም ልጁ ባለጌ ነው (ነች) የተከለከለ ዕጽ ይወስዳል (ትወስዳለች) በሚል የሀገር ጉዳይ ሳይሆን በቤተሰብ ጉዳይ ድረስ በመውረድ ግለሰቡ ከፖለቲካ ውጪ እንዲሆን ይደረጋል ። ያም ማለት ነገሩን ጠለቅ አድርጎ ለተገነዘበ በግለሰቡ የግል ህይወት የመግባት ፍላጎት ኖሮቸው ሳይሆን ግለሰቡ ቤተሰቡን በስነ ስርአት ማስተዳደር ካልቻለ እንዴት አድርጎ ሀገርና ህዝብ ሊያስተዳድር ይችላል በሚል መርሆ ተመርኩዘው ነው ። ታዲያ እነዚህ ናቸው ለኛ ሥልጡንና ያልሰለጠነ ፖለቲካ ብለው ሊሰብኩን የሚዳዱት? እውነት እንዴት ተቀለደ ጎበዝ? ይልቁንም ስልጡን ፖለቲካውን ማስተማሩን ወደጎን ገፋ አድርገው ፣ ህዝብ በይገባኛል የሚጠይቀውን ይቅርታ በአግባቡ ሊሰጡት ይገባል ። ህዝብም ከሁሉ አስቀድሞ ይቅርታ ልንጠየቅ ይገባል ማለቱ ሲያንሰው እንጂ አይበዛበትም ።

በሀገራችን የፖለቲካ ውጣ ውረድ ውስጥ ለረዥም ዘመናት የገዢው መደብ በዳይ ፤ ሰፊው ህዝብ ተበዳይ ፤ በመሆን ከገዢ ገዢ ሲፈራረቅበት በአይነታቸው ይሄ ነው የሚባል አይነተኛ ለውጥ ሳያይባቸው አብረው ለዘመናት ተጉዘዋል ፤ በመሀከላቸውም በዳዩ ክፍል ህዝብን በደልኩ ብሎ ይቅርታ የጠየቀበት ወቅት አልነበረም ፤ ተበዳይም ተበድያለሁ ብሎ ይቅርታ ልጠየቅ ይገባኛል ብሎ የተነሳበት ጊዜ በታሪክ ተመዝግቦ አላየንም ፤ ሁለቱም ወገኖች በመሀከላቸው ቅሬታ ቢኖርም ለሀገር አንድነት ፣ ለፀጥታና ለጠላት በር ላለመክፈት ሲባል ሰፊው ህዝብ ሆደ ሰፊ በመሆን በመቻቻል ከትውልድ ትውልድ ለዘመናት አብረው ተጉዘዋል ፤ ለዚህ መቻቻል ምክንያት ሆኖ የቆየው የበደሉ አይነትና መጠን በአሁኑ ትውልድ ላይ ከተፈጸመው በደልና ግፍ በአይነቱ እጅግ የተለየና የተራራቀ በመሁኑ ነው ።

ሁሉም ነገር ማብቂያና ገደብ አለው ። ለፍቅርም ፣ ለጸብም ፣ ለበደልም ልክና መጠን አለው ፤ በነዚህ ግለሰቦችና ግብራበሮቻቸው በነበሩት የቀድሞ ጓዶቻቸው ዛሬም በስልጣን ላይ ያሉት መዥገሮች ግን ፣ በሀገርና በህዝብ ላይ ያደረሱት በደልና ግፍ መጠኑን ያለፈ ድንበርና ወሰን የሌለው እንደሆነ ፣ አገር ያወቀውና ጸሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው ። ከፋሽስትም ፋሽስታዊ ስራ ፣ የሰሩና የፈጸሙ እንደሆነ ለኢትዮጵያዊው መንገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል ።

በዘመናችን ያሉት ገዢዎች ከዚህ ቀደም በሀገርና በህዝብ ላይ በደል አድርሰዋል ከሚባሉ የቀድሞ ገዢዎች ለየት የሚያደርጋቸው በርካታ ሁኔታዎች አሉ ።

ከነዚህም ታላላቅ ልዩነቶቻቸው ከብዙው በጥቂቱ ለመጥቀስ ያሁኖቹ ገዢዎች ወይንም ከገዢው ቡድን ጋር አባሪና ተባባሪ በመሆን ተጠያቂነት ያለባቸው ግለሰቦች አገር ያስገነጠሉ ፤ ህዝብን በብሄርና በጎሳ የከፋፈሉ ፤ አንዱን ጎሳ ባንዱ ጎሳ ላይ እንዲነሳ በማድረግ የእርስ በርስ ፍጅት የፈጠሩ ፤ አንድን ጎሳ ወይንም የህብረተሰብ ክፍል ላይ የዘር ማጥፋት እርምጃ ያካሄዱ ፣ ወይንም በድርጊቱ የተባበሩ በመሆናቸው ፣ ከነሱ በፊት ከነበሩ የቀድሞ የገዢዎች በጣም የተለዩ ያደርጋቸዋል ።

ይህ የተጠቀሰው በደልና ወንጀል ከብዙ በጥቂቱ እንዲያው ለአብነት የተጠቀሰ እንጂ ፣ ወንጀላቸው በዚህ ጽሁፍ ተጽፎና ተዘክሮ የሚያልቅ ሆኖ አይደለም ። የዚህ ጽሁፍ አቀራረብ ከበደላቸው ጋር ሲነጻጸር "ውቅያኖስን በጭልፋ" እንደሆነ አንባቢያን ይረዱታል ፤ ያውቁታል ።

ስለሆነም አሁን ህዝባዊውን ትግል ተቀላቅለን ፣ የበደልነውን ሀገርና ህዝብ እንክሳለን ብለው ከተነሱ ፤ በቅድሚያ የኢትዮጵያን ህዝብ ባለፉት የስልጣን ዘመናቸው ላደረሱበት ግፍና ሰቆቃ በአግባቡ ይቅርታ ሊጠይቁትና ፣ የፈጸሙትንም በደልና ወንጀል አንድም ከህዝብ ሳይሸሽጉ

ለህዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በማቅረብ ህዝብን ይቅርታ መጠየቅ ተቀዳሚ ተግባራቸው ሊሆን ይገባል ፡፡

የቀድሞ ስራቸውና ተግባራቸውም ትክክል እንዳልነበረና የነበሩበትም ስርአትም ሆነ ያገለግሉት የነበረውን ቡድን የዘር አወቃቀርና አሰራር ሊወገዝ እንደሚገባው በመግለጽ እነሱም ለማውገዙ ግንባር ቀደም ሆነው መውጣት እንዳለባቸው ሊያውቁት ይገባል ፡፡ የህዝብን ትግል ከመቀላቀላቸው በፊት ህዝብ በእውነት መጸጸታቸውን አምኖ ሲቀበላቸው ያኔና ያኔ ብቻ ይሆናል ህዝባዊውን ትግል መቀላቀል የሚችሉት ፡፡ አሁን ተፀፅተዋል ይቅርታም ጠይቀዋል ብሎ ሊቀበላቸውና ሊያስተናግዳቸው የሚችለው ፡፡

ይህ ሁኔታ ባልተፈጠረበትና በሌለበት ሁኔታ ግን ከህዝብ ጎራ ተቀላቅሎ ስልጣን ከያዘን በኋላ ህዝብ ባለፈው ስራችን ይፍረደን ማለት ፣ ተጨፈኑና እናሞኛችሁ ከማለት ያለፈ አይሆንም ፡፡ ስልጣን ይዘው ፤ መከላከያው በስራቸው ፣ፀጥታው ፣ ፖሊሱ ሁሉም መንግሥታዊ ተቃማትን በስራቸው ካስገቡ በኋላ ህዝብ ይዳኘን ማለት ከወዲሁ አለመለወጣቸውንና የቀድሞው ማንነታቸው አብሯቸው የሚጓዝ በውስጣቸው ከህዝብ ሰውረውና ደብቀም የሚያራምዱት ዓላማቸው መሆኑን ለመናገር ነብይነትን አይጠይቅም ፡፡

የቀድሞ ስራቸውንና ተግባራቸውን በሚገባ አውግዘውና ይቅርታ ጠይቀው ወደህዝብ ጎራም ቢመጡ ትግሉን ለመርዳት እንጂ የትግሉ አራማጅ አድርጎ ከፍተኛ የአመራር ቦታን መስጠት ታላቅ ስህተት ይሆናል ፡፡ ህዝብ በሆደ ሰፊነት ላለፈው በደላቸው ተጸጽተዋል ብሎ አምኖ ይቅርታ ቢሰጣቸውም ፣ ከፍተኛ የአመራር ላይ ከመፈናጠጣቸው በፊት ቃላቸውን በተግባር ተርጉመው ፣ እንደወርቅ ተፈትነው ፣ የህዝብ ወገን መሆናቸውን ከቃላት ባለፈ በተግባር ማሳየት ከቻሉ ይሆናል ፡፡ ይህ ሳይሆን ግን በየዋህነት ካናት ላይ ፊጢጥ እንዲሉ መንገዱን አልጋ ባልጋ አመቻችቶ አለጠያቂ እንዳሻቸው እንዲረማመዱ ማድረግ ግን ፣ ዳግም ሊወጡት የማይችሉት መካራ በራስ ላይ መጋበዝ ይሆናል ፡፡

አገራችን ኢትዮጵያን ለዘመናት ሲገዙ የነበሩት ከዚህ ቀደም ምን ሰርተሀል ፤ ምን ወንጀል ወይም መልካም ሥራ ሰርተሀል እና የመሳሰሉትን ዋና ዋና ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ባለመቻሉና የመጣውን ሁሉ አሜን ብሎ በመቀበሉ ዛሬም እንደቀድሞው ጠያቂ የሌላቸው አምባ ገነኖች ሲርግጡትና ሲገዙት ኖረዋል ፡፡ ይህ አይነት አካሄድ ካሁኑ ሊገታ ካልቻለ የነገዋም ኢትዮጵያ ዛሬ ካለችበት ሁኔታ አንድ ስንዝር ወደፊት መጓዝ እንደማትችል ከማንም የተሰወረ አይሆንም ፡፡ "ሞኝን እባብ ሁለቴ ይነድፈዋል" እንደሚባለው ሁሉ ተግባርን ያላከለ ቃልን ብቻ ተቀብሎና አምኖ ለዳግማዊ ጥፋት እራስን ማዘጋጀት ከስህተትም በላይ በራስ ላይ ወዶ ዳግማዊ ምጸትን መጋበዝ ይሆናል ፡፡

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል !

ከአይምሮ ዳኛቸው